የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)

# 2013 ዓ.ም. ምርጫ
# የሥነ-ምግባር መመሪያ

ታህሳሥ 2013 ዓ. ም.

# የኢትዮጵያ ዜጎች ለማህበራዊ ፍትህ

## ምርጫ 2013

## የሥነ-ምግባር መመሪያ

# ማውጫ


መነሻ ............................ 1

የምርጫ ሥነ-ምግባር መመሪያ ተፈፃሚነት ........ 5

የሥነ ምግባር መመሪያው መርህ ............... 6

የሥነ ምግባር ደንቡን ማክበር ................. 8

ሕግ ማክበር .......................... 9

የምርጫ ዘመቻ አስተዳደር.................. 10

በምርጫ ሂደት ....................... 12

የቋንቋ አጠቃቀም፤ .................... 14

የምልክት አጠቃቀም፤ .................. 16

ማዋከብ፣ ፀበኝነትና ሃይልን መጠቀም ........... 17

ሀላፊነትን ያለአግባብ መጠቀም ............. 19

የሙስና/ጉቦ ተግባራት .................... 20

መልካም ግንኙነት መፍጠር ................ 21

ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ውጤትን መቀበል .......... 22

የኢዜማ 2013 ዓ.ም ሀገራዊ፣ ክልላዊና የአስተዳደር ምክር ቤቶች ምርጫ፤ የሥነ-ምግባር መመሪያ ሰነድ ተፈጻሚነት፤ .................................. 23
የኢዜማ የምርጫ 2013 ሥነ-ምግባር ሰነድ፤ በኢዜማ የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴና የብሄራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዓባላት ቀርቦ በጸደቀው መሰረት፣ ከታህሳስ 9 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ ተፈጻሚ ሆኗል። ............................. 24

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 1

## መነሻ

ኢዜማ፣ የ2013 ዓ.ም. ምርጫ ምንም እንኳን የአለም አቀፍ፣ ምርጫ ነጻ እና ፍትሃዊ መሆኑን የሚያረግግጡ መለኪያዎች በሙሉ ባለንበት ተጨባጭ ሀገራዊ ሁኔታ ማሟላት ባይቻልም ፣ ከዚህ በታች የተቀመጡትን አራት መሰረታዊ መመዘኛዎች ማለትም፡-

1. ተፎካካሪ ድርጅቶች በየትኛውም የሀገሪቷ አካባቢ ያለገደብ መንቀሳቀስ መቻል፤
2. መራጩ ሕዝብ ሳይፈራ በነጻነት የፈለገውን ተፎካካሪ የሚመርጥበት ሀገራዊ ድባብ መኖር፤
3. ከምርጫው ጋር ግንኙነት ያላቸው የምርጫ ቦርድን ጨምሮ የፌደራልም ሆነ የክልል መንግስታት ተቋማት ተፎካካሪዎችን በዕኩልነት ማስተናገድ፤
4. የሕዝብ ድምጽ በአግባቡና በታማኝነት መቆጠር፣

ማሟላት ከቻለ፤ ከዚህ በታች የተቀመጡትን ምክንያቶችን ፡-

1. በታሪካችን ለመጀመሪያ ጊዜ የሕዝብ የምርጫ ፍላጎት ተግባራዊ ሊሆን የሚችልበት፣ ኢዜማን ጨምሮ በቁልፍ ባለድርሻዎች ላይ ፍላጎት መኖሩ፤
2. በሀገራችን የሚገኙ ሀገራዊና ክልላዊ ፓርቲዎች ከህዝብ ሊኖራቸው የሚችለውን ድጋፍ በሰለጠነ የምርጫ ሂደት ውጤት ማወቅ የሚችሉበት ጥሩ አጋጣሚ መሆኑ፤
3. የ2013 ምርጫ "እንከን የለሽ" እንኳን ባይሆን፣ ተቀባይነት ባለው ሂደትና ውጤት ሊጠናቀቅ የሚችልበት እድል መኖሩ፣ በእርግጥም ከዚህ በፊት ማድረግ ያልተቻለውን ማድረግ እንደሚቻል ማሳያ የመሆን እድል ያለው መሆኑ፤
4. ወደፊት ለሚደረጉ ምርጫዎች ተጨባጭ ልምዶች ማግኘት የሚቻልበት መልካም አጋጣሚ መሆኑ፤
5. በምርጫ አሸናፊ ሆኖ የሚወጣው ድርጅት ከዚህ በፊት በታሪካችን ከነበሩት መንግስታት በሙሉ ሕጋዊ ቅቡልነት ያለው አካል ሊሆን የሚችልበትንም አጋጣሚ መፍጠሩ፤

6. በምርጫው የተለያዩ የሕዝብን ፍላጎቶች ሊያንጸባርቁ ለሚችሉ ድርጅቶች የመሳተፍ ዕድል የሚሰጥ መሆኑ፤
7. የተለያዩ የሕዝብ ፍላጎቶች በክልልም ሆነ በፌደራል ፓርላማው ሊሰሙ የሚችሉበትን ዕድል መፍጠር የሚችል መሆኑ፤
8. ተቀባይነት ያለውን የምርጫ ሂደትና ውጤት መሰረት አደርጎ የሚቋቋመው መንግስት፣ የኢትዮጵያን ጥቅምና ደህንነት በሚመለከት ከማናቸውም ሦስተኛ አካል ጋር የሚያደርገውን ከህጋዊ ቅቡልነት የሚመነጭ፣ ጠንካራ አቅም ማግኘት የሚችልበትን ዕድል መፍጠር መቻሉን፤

ታሳቢ በማድረግ፣ ኢዜማ፣ የ2013 ምርጫ፣ አሁን ሀገራችን ያለችበትን አስቸጋሪና አደገኛ ሁኔታ ወደ ተረጋጋ ሀገራዊ ሁኔታ የመቀየር እና የተጀመረውን ለውጥ በጠንካራ መሰረት ላይ እንዲቆምና እንዲቀጥል ማድረግ የሚቻልበትን መልካም አጋጣሚ ከመፍጠር አንጻር፣ **እጅግ ከፍተኛ የሆነ ሀገራዊና ታሪካዊ ፋይዳ እንዳለው፣ ከልቡ ያምናል።**

ኢዜማ ለምርጫ 2013 የሰጠውን ከፍተኛ ሀገራዊና

ታሪካዊ ፋይዳ እውን ለማድረግ መውሰድ ከሚገባው ሀላፊነቶች መሀል፣ የኢዜማ አመራሮች፣ ዕጩዎች፣ ዓባላትና ደጋፊዎች ልንተገብራቸው የሚገቡ መልካም ሥነ-ምግባራትና ማድረግ የሌሉብን ተግባራት በግልጽ ማስቀመጥ በመሆኑ፣ ይህ የምርጫ 2013 የሥነ-ምግባር ዝርዝር መመሪያ፣ በኢዜማ የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴ ተዘጋጅቶ ቀርቧል።

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 2

# የምርጫ ሥነ-ምግባር መመሪያ ተፈፃሚነት

1. ከብሄራዊ የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዓባላት ጀምሮ እስከ ምርጫ ወረዳ የአመራር አካላት ድረስ፣ በየደረጃው የሚገኙ የአመራር አካላት፤
2. ከምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመት ኮሚቴ ጀምሮ እስከ ምርጫ ወረዳ የምርጫ ዘመቻ አስተባባሪ ኮሚቴ በየደረጃው የሚገኙ የምርጫ ዝግጅትና ዘመቻ አካላት፤
3. የኢዜማ የሕዝብ ተወካዮች፣ የክልልና የአስተዳደር ምክር ቤቶች እጩዎች፤
4. የኢዜማ መላው ዓባላትና ደጋፊዎች፤

ላይ ተፈጻሚነት ይኖረዋል፤

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 3

# የሥነ ምግባር መመሪያው መርህ

1. የመንግሥት ሕጋዊ ቅቡልነት መሰረት በዴሞክራሲያዊ መንገድ በመድብለ ፓርቲ ሥርዓት በሚደረግ ምርጫ ብቻ ነው። በሌላ መንገድ የሚገኝ ወይም የሚያዝ ሥልጣን ህጋዊ ቅቡልነት አይኖረውም። ይህም፡-

   I. በምርጫ ውድድር ወቅት የፖለቲካ ፓርቲዎች እና ዕጩዎቻቸው አማራጭ ፖሊሲዎችን ለመራጮች በማቅረብ መራጮች በመረጃ ላይ ተመስርተው ውሣኔ እንዲሰጡ ማገዝ ይኖርባቸዋል፤

   II. መራጮች በነፃነት፣ ያለማንም ጣልቃ ገብነት፣ ያለፍርሃት እና መደለል መምረጥ መቻል አለባቸው፤

2. ይህን የሥነ-ምግባር መመሪያ ሁሉም የኢዜማ አባላት፤ ተወዳዳሪዎች እና ደጋፊዎች ራሳቸውን ለዚህ ሥነ ምግባር መመሪያ በማስገዛት፤ በቅንነት ለመተግበር የሚከተሉትን ማድረግ ይኖርባቸዋል፦

   I. ይህ የሥነ-ምግባር መመሪያ እራሳቸውም አክብረው ሌሎችም እንዲያከብሩ ማድረግ ይኖርባቸዋል፤

   II. ምርጫው፣ የመራጩን ሕዝብ ነጻ የምርጫ ፍላጎት፤ ማንጸባረቁን ማረጋገጥ ያስፈልጋል፤

   III. በብሔራዊ ምርጫ ቦርድ የተረጋገጠው የመጨረሻው የምርጫው ውጤት ተቀባይነት ይኖረዋል፤

ኢዜማ

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 4

# የሥነ ምግባር ደንቡን ማክበር

1. የኢዜማ አባላት፤ በየደረጃው የሚገኙ አመራሮችና ዕጩ ተወዳዳሪዎች፦

   I. በዚህ የሥነ-ምግባር ደንብ ይገዛሉ፤

   II. የሥነ ምግባር መመሪያው በመሪዎች፤ ተወዳዳሪዎች፤ ታዛቢዎች፤ በአባላት እንዳይጣስ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋሉ፤

   III. ቅሬታ የማቅረብ መብታቸውን በተሳሳተ መረጃ፤ በፈጠራ ክስ በመሳሰሉት ያለ አግባብ አይጠቀሙም፤

2. የፓርቲ መሪ/ሊቀመንበር በየደረጃ ለሚገኙ የፓርቲ አባላት፤ ደጋፊዎችና ተወዳዳሪዎች የሥነ-ምግባር መመሪያውን እንዲያከብሩ እና መመሪያውን ተግባራዊ እንዲያደርጉ ዝርዝር የአፈፃፀም መመሪያ/ትዕዛዝ ያስተላልፋሉ።

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 5

# ሕግ ማክበር

የኢዜማ አባላት በሙሉ ይህን የሥነ-ምግባር መመሪያ፣ የፓርቲዎችን የቃል ኪዳን ሰነድ፣ የሀገሪቱን የምርጫ ሕጎችና ደንቦችን በሙሉ ያከብራሉ።

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 6

# የምርጫ ዘመቻ አስተዳደር

1. የኢዜማ አባላት

   I. የሌሎች ፓርቲዎችን የምርጫ ቅስቀሳ ማድረግ፤ አማራጭ ሃሳባቸውን እና መርሆዎቻቸውን የማቅረብ መብታቸውን ያከብራሉ፤

   II. በጨዋነት የሌሎችን ፓርቲዎች፣ መራጮች፣ ሕዝብና በምርጫ ክልል ያለውን ማሕበረሰብ መብት ባከበረ መልኩ ይንቀሳቀሳሉ፤

   III. የሚዲያዎችን ነፃነትና ገለልተኝነት ያከብራሉ፤

   IV. የምርጫ ክልል ቢሮዎችን ለመራጮቹ ክፍት በማድረግ ያስተናግዳሉ፤

   V. መራጮች በፖለቲካ በንቃት ለመሳተፍ ያላቸውን ፍላጎት ሊተገብሩ የሚችሉበትን እድል ያመቻቻሉ፤

2. የኢዜማ አባላት የሚከተሉትን ተግባራት አያደርጉም፤

   I. ሚዲያዎችና አባላቶቻቸውን ማንጓጠጥ፤ ሥራቻውን እንዳይከውኑ እንቅፋት መሆን፤ ሌሎች ፓርቲዎችን ማወከና ፍርሓት እንዲሰማቸው ወይም ንብረታቸው እንዲጎዳ አያደርጉም፤
   II. በራሪ ወረቀቶች፤ ፖስተሮች እንዳይሰራጩ አያደርጉም፤
   III. የሌሎች ፓርቲዎችን ፖስተርና የቅስቀሳ ቁሳቁስ አያበላሹም፤
   IV. ስብሰባዎችን፣ ሠላማዊ ሰልፎችንና ህዝባዊ እንቅስቃሴዎችን አይገድቡም፤ አያውኩም፤
   V. ግለሰቦች በሌሎች ፓርቲዎች ዝግጅቶች እንዳይገኙ እንቅፋት አይሆኑም፤
   VI. አባሎች የተከለከሉ ነገሮች እንዲፈፅሙ አይፈቅዱም/አያበረታቱም፤

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 7
# በምርጫ ሂደት

1. ኢዜማ

   I. ከምርጫ አስፈጻሚ ሀላፊዎች ጋር በመተባበር ሠላማዊና ሥርዓት ያለው ምርጫ እንዲደረግ እና መራጮች ምርጫቸውን ያለምንም መደናቅፍ እንዲያካሂዱ ያደርጋል፤

   II. የምርጫ አስፈፃሚዎች ደህንነት ከምርጫ በፊት፣ በምርጫው ዕለትና ከምርጫ በኋላ እንዲጠበቅ የበኩሉን ያደርጋል፤

   III. ተገቢውን ክብር በመስጠት ከምርጫ አስፈፃሚዎች ጋር ይተባበራል፤

   IV. የምርጫው ሚስጥራዊነት እንዲጠበቅ ያደርጋል፤

2. ኢዜማ

I. በሕገ ወጥ መንገድ የምርጫ ጣቢያ በመውረር ወይም በጥቅማ ጥቅም መራጮች ላይ ጫና አያደርግም፤
II. በምርጫ ቆጠራ ወቅት የምርጫ አስፈፃሚዎች ላይ ምንም ዓይነት ሕገ ወጥ ተግባር ወይም ጫና አይፈጽምም፤
III. ከመራጮች ሚስጥራዊ ድምጽ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የተሳሳተ መረጃ አይሰጥም፤

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 8

## የቋንቋ አጠቃቀም፤

ኢዜማ አባላት፣ አመራሮች እና ዕጩዎች፦

1. በምርጫ ዘመቻ፣ በምርጫው ቀንና በድህረ ምርጫ ወቅት በጨዋነትና ሠላማዊ ድባብ በሚፈጥር መልኩ አደራጅተው መልዕክቶችን ማስተላለፍ ይኖርባቸዋል፤
2. ሃላፊነት እና ክብርን ባረጋገጠ ደረጃ ቋንቋን መጠቀም ይኖርባቸዋል፤
3. በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት ንግግር የሚያደርጉ የፓርቲ አባላት፦

   3.1. ግጭት የሚያነሳሱ ወይም ሌሎችን የሚያንቋሽሹ ወይም የተለያዩ ማስፈራራያዎች፣ በማንኛውም ዓይነት መልኩ በየትኛውም ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ መፈፀም የለባቸውም፤

**3.2** **የኢዜማ አባላትና አመራሮች፣ ግጭት ቀስቃሽ ቃላቶችና ፅሑፎችን በማንኛውም ዓይነት በራሪ ወረቀት፣ ፖስተሮች፣ ሌሎች መንገዶች በግልፅ ወይም በስውር ፈጽሞ ማሰራጨት የለባቸውም፤**

ኢዜማ

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 9

# የምልክት አጠቃቀም፤

የኢዜማ አባላት፣ አመራሮች እና ዕጩዎች፦

1. የሌሎች ፓርቲዎችን ምልክቶች አስመስሎ መጠቀም የለባቸውም፤
2. የሌሎች ፓርቲዎችን የቅስቀሳ ቁሳቁስ መውሰድ፣ ማበላሸት ወይም ማጥፋት ፈጽሞ የተከለከለ ነው፤
3. አባላትና ደጋፊዎችን ምልክት አጠቃቀምን በሚመለከት 10.1 እና 10.2 የተጠቀሱትን መደረግ የሌለባቸው ተግባራት እንዲሰሩ አይፈቅዱም፤

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 10

## ማዋከብ፣ ፀበኝነትና ሃይልን መጠቀም

የኢዜማ አባላት፣ አመራሮች እና ዕጩዎች፦

1. በምንም ዓይነት ሁኔታ ግምት ውስጥ መግባት ወይም ሌሎችን ማዋከብ የለባቸውም፤
2. ግጭት ወይም የግጭት ስጋቶች እንዳይፈጠሩ፣ የሕዝብ ሠላም ስጋት ላይ እንዳይወድቅ አስፈላጊውን ሁሉ ማድረግ ይኖርባቸዋል፤
3. የሌሎች ፓርቲዎች አባላትን ሰብአዊ መብት እና ንብረት ማክበር ይኖርባቸዋል፤
4. የኢዜማ መሪዎች፣ ዕጩ ተወዳዳሪዎች፣ አባላትና ደጋፊዎች ምንም ዓይነት የጦር መሣሪያ፤ (ዘመናዊም ሆነ ባህላዊ) በምርጫው ሂደት ውስጥ በየትኛውም አካል በሚካሄዱ ስብሰባዎች ላይ ይዞ መገኘት ፈፅሞ ክልክል መሆኑን በግልጽ ሊያውቁ ይገባል፤

5. የኢዜማን ጥንካሬና የበላይነት ለማሳየት ምንም ዓይነት የሀይል እንቅስቃሴ ላይ አይሳተፉም፣ አይፈቅዱም፤
6. በሕዝብ ወይም በግለሰቦች ንብረት ላይ ጉዳት አያደርሱም፤ ወይም ደጋፊዎች ይህን እንዲያደርጉ በምንም ዓይነት ሁኔታ አይፈቅዱም፤

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 11

## ሀላፊነትን ያለአግባብ መጠቀም

1. በየደረጃው ያሉ የኢዜማ አመራር አባላት ሃለፊነት የሚሰጣቸውን አቅም በመጠቀም የምርጫውን ሂደትም ሆነ ውጤት ጥያቄ ውስጥ ሊጨምር በሚችል፣ በመራጩ ሕዝብ ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ ማድረግ የለባቸውም፤
2. የኢዜማ ዕጩ ተወዳዳሪዎች የሆኑ፣ እጩነታቸው የሚሰጣቸውን አቅም በመጠቀም፣ የምርጫውን ሂደትም ሆነ ውጤት ጥያቄ ውስጥ ሊጨምር በሚችል በመራጩ ሕዝብ ላይ ምንም ዓይነት ተጽዕኖ ማድረግ የለባቸውም፤

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 12

## የሙስና/ጉቦ ተግባራት

የኢዜማ መሪዎች፣ አባላትና እጩ ተወዳዳሪዎች፦

1. መራጮች ኢዜማን እንዲመርጡ፤ ድምፅ እንዳይሰጡ ወይም ድምፀ ተዓቅቦ እንዲያደርጉ ጫና ማድረግ ወይም በገንዘብ መደለል ወይም ሌላ ዓይነት መደለያ ማቅረብ የለባቸውም፤
2. ዕጩዎች የፓርቲ ዕጩ እንዳይሆኑ ወይም ዕጩነታቸውን እንዲሰርዙ ጫና ማድረግ ወይም በገንዘብ መደለል ወይም ሌላ ዓይነት መደለያ ማቅረብ የለባቸውም፤
3. በምርጫው ሂደት የሚሳተፉ ገለልተኛ ተቋማትና የተቋማቱ ሰራተኞች አግባብ የሌለው ድጋፍ ለኢዜማ እንዲሰጡ ወይም ለሌሎች ድጋፍ እንዲነሱ ማድረግ የለባቸውም፤

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 13

## መልካም ግንኙነት መፍጠር

1. ኢዜማ ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር መልካም ግንኙነት እንዲኖረው አስፈላጊውን ጥረት ሁሉ ያደርጋል፤
2. በምርጫ ክልሎች ከሌሎች ፓርቲ ዕጩ ተወዳዳሪዎች እና ከምርጫ ቦርድ ጋር የጋራ ኮሚቴ እንዲኖር ያበረታታል፣ በቅርበት አብሮ ይሰራል፣ ይህንንም መድረክ ችግሮችን በጋራ ለመፍታት ይጠቀምበታል፤

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 14

# ነፃና ፍትሃዊ ምርጫ ውጤትን መቀበል

1. በምርጫ ቦርድ የተረጋገጠን ውጤት ይቀበላል፤
2. ቅሬታውን ለህጋዊ ቅሬታ ተቀባይ አካል ያቀርባል፤
3. በሚመለከተው አካል የተሰጠን የመጨረሻ ውሣኔን ይቀበላል፤

ኢዜማ

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 15

# የኢዜማ 2013 ዓ.ም ሀገራዊ፣ ክልላዊና የአስተዳደር ምክር ቤቶች ምርጫ፤ የሥነ-ምግባር መመሪያ ሰነድ ተፈጻሚነት፤

የምርጫ 2013 የኢዜማን የሥነ-ምግባር መመሪያ ሰነድ ተላልፎ የተገኘ ማንኛውም ዓባል፣ እጩና አመራር ጉዳይ በፓርቲው ሕገ-ደንብ ተርጓሚና ዲሲፕሊን ኮሚቴ ይታያል፣ እንደ አስፈላጊነቱም በሀገሪቷ ሕግ ሊያስጠይቅ ይችላል፤

◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆◆

# 16

## የኢዜማ የምርጫ 2013 ሥነ-ምግባር ሰነድ፤ በኢዜማ የምርጫ ስትራቴጂና ማኔጅመንት ኮሚቴና የብሄራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ዓባላት ቀርቦ በጸደቀው መሰረት፣ ከታህሳስ 9 ቀን 2013 ዓ.ም. ጀምሮ በሥራ ላይ ተፈጻሚ ሆኗል።

ኢዜማ

**የኢዜማ ብሔራዊ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ**

**ታህሳስ 2013 ዓ.ም**

**አዲስ አበባ**

ኢዜማ

**የኢትዮጵያ ዜጎች ለማኅበራዊ ፍትህ (ኢዜማ)**

ራስ ደስታ ዳምጠው መንገድ
የቀድሞ ሳይንስ እና ቴክኖሎጂ ሕንፃ

+251-944-107661
Pr@ethzema.org
www.ethzema.org
Facebook.com/ethzema
@ETHZema